ገቢ 1467
10-04-10

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር Ref.No. 7/ሄ/1/2/222
ቀን Date 5/4/2010

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ ስርዓት ተፈፃሚ እንዲሆን በጉምሩክ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን፣ ይህን አፈፃፀም የሚመራ መመሪያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያወጣ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2(24) እና 2(52) ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

ስለዚህ ይህንኑ አፈፃፀም የሚወስነውን መመሪያ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሣስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብረሃም ተከስተ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

Letter/H/E.T

1-11-155 24 00, 22 66 98
1-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 09 24,65
251-11-155 11 ...
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa- Ethiopia

እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

# የግል መገልገያ ዕቃዎች መመሪያ ቁጥር 51/2010

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

በአየር መንገድም ሆነ በየብስ ከውጭ አገር የሚመጡ መንገደኞች፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን እና በተለያዩ ሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥረዉ የሚመጡ ትዉልደ ኢትዮጵያዊያን ወይም የዉጭ አገር ዜጎች፣ መንግስት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሰረት የሚመጡ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ አትዮጵያዊያን ወይም የውጭ አገር ዜጎች የሚስገቧቸው እና የሚስወጧቸው እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር ቆይተው ጠቅለው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚያስገቧቸውን ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ እቃዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈል በሚመለከት ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ለንግድ የማይውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ቀረጥና ታክስ አወሳሰን በሚመለከት ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ ስርዓት ተፈጻሚ እንደሚሆን በጉምሩክ አዋጁ የተደነገገ በመሆኑ፣

በአየር ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ መንገደኞች የሚሰጠዉን የጉምሩክ አገልግሎት ማሰለጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 2(24)፣2 (52) እና 33(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ዝርዝር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 51/2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) **"ለንግድ የማይውል ዕቃ"** ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት እና ለባለቤቱ ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ

ወይም ፍጆታ የሚውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰ ባለመብት ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ ነው።

2) **"የግል መገልገያ ዕቃ"** ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ቀረጥና ታክስ የማይከፈልበት እና ለባለቤቱ ወይም ለባለይዞታው ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተጠቀሰ ባለመብት ይዞት ወይም ከባለመብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ ነው። ።

3) **"መንገደኛ"** ማለት ማንኛውም በየብስ በኢትዮጵያ መግቢያና መውጫ በሮች ወይም በዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያዎች በኩል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ሰው ሲሆን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2) የተጠቀሱትን ባለመብቶች አይጨምርም።

4) **"ተመላሽ ኢትዮጵያዊ"** ማለት በህጋዊ መንገድ ወይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ በሚኖርበት አገር የስራና የመኖሪያ ፈቃድ አግኝቶ ሲኖር የነበረ ሆኖ ጠቅሎ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው።

5) **"በተለያዩ ሙያዎች ለማገልገል የሚመጣ"** ማለት ኢትዮጵያ ዉስጥ በሙያዉ በተለያዩ መንግስታዊ መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለምአቀፍ፣አህጉርአቀፍ ወይም አገር አቀፍ ድርጅቶች፣ ህጋዊ ማህበራት፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስትና የግል የጋራ ድርጅቶች ውስጥ ለማገልገል በህጋዊ መንገድ ተቀጥሮ ወይም በሌላ ህጋዊ ስምምነት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወይም የዉጭ አገር ዜጋ ነው ።

6) **"ወጥ የሆነ የታሪፍ መጣኔ"** ማለት ዕቃዎች ከመደበኛው የታሪፍ መጣኔ በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱበት ልዩ የታሪፍ መጣኔ ሆኖ በባህሪያቸውም ሆነ በሌላ ሁኔታ ተቀራራቢነት ያላቸውን ዕቃዎች በመለየት ለእያንዳንዱ ዕቃ ከጠቅላላ ቀረጥና ታክስ በመነሳት አማካይ የታሪፍ መጣኔ በማስላት የሚገኝ ልዩ የታሪፍ መጣኔ ነው።

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ... ሬከርድ ... ክፍል